ውድ ወላጆች

ለልጃችሁ መወለድ እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን፤ ለናንተና ለልጃችሁም ጤንነትን ደህንነትን እንመኝላችኋለን።

በስዊዘርላንድ ኑሮአችሁ የደስታና የተቃና እንዲሆን መልካም ምኞታችን ነው። ማንኛውም የስዊዘርላድ ነዋሪ የግል እምነቱን የመከተል መብት እንዳለው ልናሳውቃችሁ እንወዳለን።

በባሕላችሁ መሰረት ወንድ ልጅ ሲወለድ መገረዝ እንዳለበት እናውቃለን። ይህም ደግሞ በስዊዝ ውስጥ የተከለከለ አይደለም።

ልናስገነዝባችሁ የምንወደው ነገር ግን፡-

| |
|---|
| - ግርዛት በቤተሰብ አባል ወይም በአዋላጅ ነርሶች (ሄባመ) በኩል ማድረግ የተከለከለ ነው። |
| - ግርዛት መከናወን ያለበት በሙያው በሰለጠነ ሰውብቻ ነው መሆን ያለበት። |
| → በዶክተር በኩል ወይም ደሞ የተማረ የጁይሽ (ይሁዳ) ማሕበረሰብ „ሞሕል“ ተብሎ በሚጠራው አማካኝነት መሆን አለበት። |

**የወንድ ልጅ ግርዛት አገልግሎቶች የሚገኝበት ቦታ የት ነው?**

- ሆስፒታል፣ የግል ዶክተር ወይም ቀዶ ጠጋኝ (አድራሻቸው ከዚህ በታች እንደተገለጸው ይሆናል)

**መደረግ ያለበት ጥንቃቄ !**

- የልጃችሁ ጤና ዝተጠበቀ እንዲሆን በግርዛቱ ማግስት ቁስሉ በሐኪም እንዲታይ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ይሕንንም አንድ የግል ሐኪም ጋር ማድረግ ይቻላል (በቅድሚያ ግን ቀጠሮ መያዝ ያሻል) ወይም ደሞ ተገራዡ በጣም ልጅ ከሆነ ሄባመዎች ሊያዩት ይችላሉ (ሄባመዋ ስለጉዳዩ እንድታውቅ በቅድሚያ መንገር ያስፈልጋል)

**በጣም መተኮር ያለበት**

የሴት ልጅ ግርዛት በስዊዘርላድ (በኤርትራ) ሕግና ደንብ መሰረት የተከለከለ ነው።። ይህም ክልከላ በስዊዘርላንድ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሐገሮች የፀና መሆኑን ልናሳውቃችሁ እንወዳለን። ይህንን ሕግ መተላለፍ ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣት ወይም የዕስር ቅጣት ያስከትላል።

| **አድራሻ** | **የክፍያ መጠን** |
|---|---|
| ሐኪሞችና ዶክተሮች (በማደንዘዣ የሚደረግ ግርዛት) | |
| SoH ቦታዎች | 1500 ፍራንክ |
| የቀዶ ጥገና ማዕከል ሶሎቱርን፤ ዶ/ር ላይምግሩበር | 1200 ፍራንክ ከ3 ዓመት ጀምሮ ላሉ |
| የቀዶ ሕክምና ዶ/ር ክራፍት ኦልተን | 1400 ፍራንክ ከ2 እስከ 3 ዓመት ላሉ |
| የልጆች ሐኪምቤት - ሊስታል | 1350 ፍራንክ ከ1 ዓመት ጀምሮ |
| የጁሾች ገራዥ / ሞሕለ ያለማደንዘዣ የሚደረግ ግርዛት) | |
| ኤስራ ቫይል - ባዝል<br>Tel. 079 232 50 94<br>E-Mail: esra@weill.ch | ግርዛቱ ባዝል የሚካሔድ ከሆነ 500 ፍራንክ፤<br>ግርዛቱ ሶሎቱርን ግዛት ውስጥ ከተደረገ - እንደ ሁኔታው ይወሰናል።<br>መገረዝ የሚችሉት ከ3 ወር በታች የሆኑ ሕፃናቶች ብቻ ናቸው። |

Amharisch

Gesundheitsamt des Kantons Solothurn